# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

ከነሐሴ ፳ እስከ ፲፬ ባሉት ዕለታት እሑድ ሲውል

የቃሉ ትርጉሜ ስርወ ቃሉ ከርመ፣ ከረመ ካለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጓሜውም ወርኃ ዝናም፣ ወርኃ ነጐድጓድ፣ ዘመነ ባሕር፣ ዘመነ አፍላግ፣ ዘመነ ጠል፣ ዘመነ ደመና፣ ዘመነ መብረቅ ማለት ነው። የክረምት ዘመን ከሰኔ ፳፮ እስከ መስከረም ፳፭ ቀን ድረስ ነው።

## የዕለቱ ምስባክ

አዋልደ ንግሥት ለክብርከ
ወትቀውም ንግሥት በየማንከ
በአልባሠ ወርቅ ኡጹፍት ወሑብርት

የንግሥት ልጆች ለክብርህ ናቸው
በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋና ተሸፋፍና
ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለህ

መዝ ፵፬፥፱

ወንጌል፥ ሉቃ ፩፥፳፮-፶፮
ቅዳሴ፥ የማርያም (ጐሥዐ)

## የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

«ዛቲ ይእቲ»

### በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ዕብ ፱፥፱-፲፮ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ፪ኛ ዮሐ ፩፥፩-ፍጻሜ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፩፥፩-፲፭ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

## የዕለቱ ትምህርት

# የገብርኤል ሰላምታ

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ያቀረበላትን ሰላምታ መሰረት በማድረግ እናት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን በመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ ዘወትር ቅድስት ድንግል ማርያምን ሰላም ትላታለች። ይህ የመልአኩ ገብርኤል ሰላምታ ሞት ለተፈረደበት ለሰው ልጅ ባሕርይ ግሩም ወንጌል (የምሥራች) ነው። ከዚህ የተነሳ መልአኩን ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት ተዋህዶን የሚሰብኩ ቅዱሳን «መጋቤ ሐዲስ» የመጀመሪያው ወንጌል ሰባኪ (መምህር) ይሉታል።

ድንግል ማርያምንም በመልአኩ ሰላምታ ዘወትር ሰላም እንድንላት ሥርዓት ሠርተው አልፈዋል። ከዚህ በማስከተል ሰላምታዎቹን በዝርዝር እንመለከታለን።

### ፩) ደስ ይበልሽ (ሉቃ ፩፥፳፰)

መልአኩ ወደ ድንግል ቀርቦ መጀመሪያ የተናገረው «ደስ ይበልሽ» በማለት ነበር። ወንጌል ማለት የምሥራች ማለት ነው። የምሥራች ማለት የደስ ደስ ማለት ነው። መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልኮ በመምጣት ድንግልን «ደስ ይበልሽ» አላት። ይህ ለድንግል ማርያም ግሩም ጸጋ ነው። ምክንያቱን የአዳም ተስፋው በእርስዋ በኩል እንዲፈጸም በአዳም በኩል እግዚአብሔር ወስኗልና። ሞት የተፈረደበት ለዘመናት እንዲያለቅስ፣ እንዲፈርስ፣ እንዲበሰብስ፣ አእምሮውን ነበቡን አጥቶ በሰው ትከሻ ተጓጉዞ ወደ መቃብር እንዲጣል የተፈረደበት የሰው ልጅ ባሕርይ በድንግል ማርያም በኩል ደስ ይበልህ ተባለ። ስለዚህ የሰው ዘር በሙሉ የድንግል ደስታ ደስታው ስለሆነ «ምልእተ ጸጋ ደስ ይበልሽ» እያለ ይዘምርላታል። ድንግል የደስታ መፍሰሻ እንድትሆን በአልቃሻው ዓለም ውስጥ እግዚአብሔር ወስኗልና። በመሆኑም ድንግል ማርያምን ደስ ይበልሽ እያለች ቤተ ክርስቲያን የምታመሰግንባቸውን ቃላት እንመልከት። ቅዱስ ኤፍሬም የመልአኩን ሰላምታ መሠረት በማድረግ «ተፈሥሒ ኦ ቤተ ልሔም ሀገሮሙ ለነቢያት - የነቢያት ሀገራቸው ቤተ ልሔም ደስ ይበልሽ» (የሰኞ ውዳሴ ማርያም) «ተፈሥሒ ኦ ወላዲተ እግዚእ ሃሴቶሙ ለመላእክት - የመላእክት ተድላ ጌታን የወለድሽ ደስ ይበልሽ» ወዘተ እያለ እመቤታችንን ሰላም ብሏታል። እኛም በውዳሴው ደስ ይበልሽ በማለት ሰላምታ እናቀርባለን።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ለድንግል ያለውን ክብር ሲገልጽ «እግዚአብሔር ቃል ነፍስን ሥጋን ከአንቺ ነስቶ ሰው የሆነ ሙሽራ ከጫጉላው እንዲወጣ ከአንቺ የተገኘ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ ... የጠፋ በግ አዳምን የፈለገው ቸር ጠባቂ ከአንቺ የተገኘ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ፣ ከአንቺ ያደረ ምድር ቅድስት ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ፣ አማኑኤልን የወለድሽ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ ... ወዘተ» በማለት ያመሰግናት እንደነበር ተጽፏል። (ሃይማኖተ አበው ዮሐንስ አፈወርቅ ገጽ ፪፻፶፫ ክፍል ፳፮ ቁጥር ፵፭-፵፱)።

ቤተ ክርስቲያንም «ሙሐዘ ፍስሐ-የደስታ መፍሰሻ» በማለት ታመሰግናታለች፣ ቅድስት ድንግል ማርያም

# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

ከነሐሴ ፳ እስከ ፲፬ ባሉት ዕለታት እሑድ ሲውል

## የገብርኤል ሰላምታ ...

በመልአኩ ብሥራት በግብረ መንፈስ ቅዱስ ቃለ እግዚአብሔር ወልድን ከጸነሰች በኋላ «ተአብዮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር ወትትሐሠይ መንፈስየ በአምላኪየ ወመድኃኒየ - ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች» በማለት ደስታዋን ገልጻለች። ለድንግል ማርያም የሆነው ደስታ ሁሉ የሰው ልጆች ደስታ ነው። በድንግል ማርያም በኩል ደስታ ለሰው ሁሉ ስለደረሰ ድንግል ማርያም የደስታ መፍሰሻ ናት። መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ደስታ እንዴት ወደ ፍጥረት ሁሉ እንደደረሰ ሲገልጽ ጌታ ሲወለድ በጨለማ ለነበሩ እረኞች «ለሕዝብ ሁሉ ታለቅ ደስታ እንደሚሆን የምሥራች እንነግራችኋለንና አትፍሩ» እንዳሏቸው ይነግረናል። ቅዱስ ጳውሎስም የድንግልን ልብ በደስታ በሐሴት የሞላው ክርስቶስ ለእኛም ተድላ ደስታ መሆኑን ሲጠቁም «ሁል ጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ ደግሜ እላለሁ ደስ ይበላችሁ» (ፊልጵ ፬፥፬) በማለት ጽፎልናል። ተፈሥሒ ተፈሥሒ እያለ ያመሰገናት ቅዱስ ኤፍሬም የድንግል ማርያም ደስታ የሰው ሁሉ መሆኑን ሲጽፍ «ተፈሣሕ ወተሐሰይ ኦ ዘመደ እጓለ እመሕያው እስመ አፍቀሮ እግዚአብሔር ለዓለም ወመጠወ ወልዶ ዋሕደ ከመ ይኅየው ኩሉ ዘየአምን ቦቱ እስከ ለዓለም - በእርሱ የሚያምን ሁሉ እስከ ዘለዓለም ይድን ዘንድ ልጁን እስከመስጠት ድረስ ዓለሙን እግዚአብሔር ወዶታልና የሰው ልጅ ሁሉ ደስ ይበልህ» አለ። እንዲሁም «ትትፌሣህ ወትትሐሠይ ኩሉ ነፍስተ ሰብእ - የሰው ልጅ ሰውነት ሁሉ ፈጽሞ ደስ ይላታል» አለ። እንግዲህ ከላይ እንደተመለከትነው ድንግልን ደስ ይበልሽ የማይል በአዳም የተነጠቀው ተድላ ነፍስ በክርስቶስ ያልተመለሰለት ብቻ መሆን አለበት። ድንግልን ደስ ይበልሽ ባልን ቁጥር እኛም የተድላ የደስታዋ ተካፋይ መሆናችንን ተገንዝበን በገብርኤል ሰላምታ ደስ ይበልሽ እንላለን።

### ፪) ሰላምታ «ጸጋን የተሞላሽ ሆይ»

መልአኩ ጸጋ እግዚአብሔር ለአንቺ ምሉዕ ሆኗልና ደስ ይበልሽ በማለት አከበራት። ፍጥረት ሁሉ እንደሚያውቀው የሰው ልጅ ከጸጋ እግዚአብሔር ተለይቶ ሐፍረቱን የሚሸፍንለት አጥቶ ይንገላታ እንደነበር ግልጽ ነው። የሰው ልጅ በኃጢአት ምክንያት ሕይወቱን አጥቷል። ኤደን ገነትን አጥቷል፤ ፍጹም ከጸጋ እግዚአብሔር ተራቁቷአል፤ አሁን ግን በቅዱስ ገብርኤል በኩል የምንሰማው ከሰው ልጆች መካከል አንዷ ለሆነች ለሰው ልጆች የባሕርይ መመኪያ ለድንግል ማርያም «ጸጋን የተሞላሽ» በማለት ሲያበስራት ስንሰማ ያስደስታል። ይህ ጸጋ በድንግል ማርያም ሳይወሰን ለፍጥረት ሁሉ ይደርሳልና።

ድንግል ማርያም ምልዕተ ጸጋ ናት። ጸጋውም ለፍጥረት ሁሉ ከተሰጠው ጸጋ ይበልጣል። ከነቢያት ጸጋ የድንግል ማርያም ጸጋ ይበልጣል። እነርሱ ስለ እግዚአብሔር ሰው መሆን ተናገሩ - እርስዋ ግን በጥበበ እግዚአብሔር እርሱን ወለደችው። ከሐዋርያትም የድንግል ጸጋ ይበልጣል። እነርሱ ከእርሷ የተወለደውን ኢየሱስ ክርስቶስን ለፍጥረት ሰበኩ - እርሷ ግን ወልዳ አሳደገችው። ከቤተ ክርስቲያን ጸጋ የድንግል ጸጋ ይበልጣል። ለቤተ ክርስቲያን ልሳን፣ ትንቢት፣ ስብከት .... ተሰጥቷል። ድንግል ባለቤቱን ጸንሳ ወለደችው፤ በእርስዋ በኩል የመጣው የእግዚአብሔር ጸጋ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ሁሉ ተሰጠ። ኢሳይያስ «ሕፃን ተወለደ ለነ ወልደ ተውህበ ለነ» አለ። ማለትም «ሕፃን ተወለደልን ወንድ ልጅ ተሰጠን» (ኢሳ ፱፥፮)። ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ዘር የተቀበለበት እጁ ድንግል ናት። የሰው ልጅ ባሕርይም በድንግል ተጀምሮ በእርሷ ጸጋ የተሰጠው በመሆኑም የፍጥረት ሁሉ የባሕርይ መመኪያ እመ አምላክ ሆነች።

### ፫) ጌታ ከአንቺ ጋር ነው። (ሉቃ ፩፥፳፰)

ሦስተኛው የሰላምታ ቃል እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው የሚል ነው። ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን በረድኤት እንጂ በኩነት ከሰው ጋር ያልነበረ አምላክ በአዳምና በሔዋን በደል ከሰው የተለየ አምላክ «ከአንቺ ጋር ነው» የሚለው ሰላምታ መንፈስን የሚፈውስ ነው። አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ ከአብ የተወለደ ወልድ ከድንግል ሥጋን ነፍስን መንፈስን ነስቶ ስለተወለደ እግዚአብሔር በተለየ ሁኔታ ከድንግል ጋር ነበር። ከድንግል ጋር እንደሆን የተነገረው የሰላምታ ቃል ለእኛም ጭምር ስለሆነ የመልአኩን ሰላምታ «እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነውና ደስ ይበልሽ» እያልን ለድንግል ስናሰማ እኛም ደስ ይለናል (ኢሳ ፯፥፲፬)። ከድንግሊቱ የሚወለደው አማኑኤል ይባላል በተባለው መሰረት ሲወለድ አማኑኤል ተባለ። አማኑኤል ማለት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ማለት ነው። ከድንግል ጋር የሆነ ጌታ ከእኛም ጋር ነውና ደስ ሊለን አግባብ ነው። በስሙ ስንሰበሰብ (ማቴ ፲፰፥፳)፤ እስከ ዓለም ፍጻሜ ከእኛ ጋር ነውና (ማቴ ፳፰፥፳፰-፳፱)። ይህ ብሥራት ለድንግል መነገሩ የድንግል ባሕርይ ባሕርያችን ነውና የእኛም ብሥራታችን ነው። ይህንንም ቅዱስ ኤፍሬም «ዓቢይ ውእቱ ክብር ዘተውህበ ለከ ኦ ገብርኤል መልአክ ዜናዊ ፍሱሐ ገጽ ሰበከ ለነ ልደተ እግዚአ ዘመጽአ ተቤነ» ማለትም «ወደ እኛ መጣ የጌታን ልደት የሰበከልን ፍሱሐ ገጽ መልአክ ገብርኤል ሆይ የተሰጠህ ክብር ታላቅ ነው» ማለት ነው። ቅዱስ ኤፍሬም «ሰበከ ለነ» ማለቱ ልደቱ ብሥራቱ የሰው ልጅን ሁሉ እንደሚመለከት ለመግለጽ ነው። ከድንግል የተወለደው ልዑል አምላክ ከእኛ ጋር ነውና ደስ ይበለን። እኛም ድንግልን «እግዚአብሔር ምስሌኪ» እያልን ሰላም እንበላት። በሌላም ገጽ ቅዱስ ኤፍሬም የመልአኩ ቃል

# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

## የገብርኤል ሰላምታ …

ከነሐሴ ፳ እስከ ፲፬ ባሉት ዕለታት እሑድ ሲውል

(ብሥራት) ለሕዝብ ሁሉ መሆኑን ሲገልጥ «ተፈሥሒ እስመ ተወከፍኪ ቃሎ ለመልአክ ፍስሐ ኩሉ ዓለም - የዓለሙን ሁሉ ተድላ ደስታ የመልአኩን ቃል ስለአመንሽ ደስ ይበልሽ» አለ።

### አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ (ሉቃ ፩፤፳፰)

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው ደስ ይበልሽ ካለ በኋላ የተናገረው ሰላምታ «የተባረክሽ ነሽ» የሚል ነበር። የሰው ዘር በመጀመሪያዎቹ ሰዎች በደል ምክንያት «በጸነስሽ ጊዜ ጭንቀትሽን እጅግ አበዛለሁ በጭንቅ ትወልጃለሽ … ምድር ከአንተ የተነሳ የተገረመች ትሁን በሕይወት ዘመንህ በድካም ከእርሷ ትበላለህ እሾህና አሜከላን ታበቅልብሃለች የምድርም ቡቃያ ትበላለህ ወደመጣህበትም መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ» ተብሎ ተረግሞ ነበር (ዘፍ ፫፤፲፯-፳፩)። ይህ ከባድ መርገም በሰው ሕይወት እንዲበዛና እንዲከሰት ምክንያት የሆነውን አውሬ እራስ የሚቀጠቅጥ ልጅ እንደሚወለድ ለአዳም እግዚአብሔር ቃል ገባለት (ዘፍ ፫፤፲፭-፲፯)። ለአብርሃም ደግሞ በዘሩ የምድር አሕዛብ ሁሉ እንደሚባረኩ ተስፋ ሰጠው (ዘፍ ፲፪፤፬)። ለይስሐቅም ለያዕቆብም ለአበውም ሁሉ ይህ ቃል ኪዳን ተሰጣቸው። በመጨረሻ ላይ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስን የሚያስወግድ የእባቡን እራስ የሚቀጠቅጥ ቡሩክ የማሕጸንዋ ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚወለድባት ቅድስት ማርያም ቡሩክት ነሽ ተባለች። ቡሩክት ማለትም መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለባት የበረከት እናት ማለት ነው። የማሕጸንዋ ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስም ቡሩክ ነው፤ ቡሩክ ይባላል (ሉቃ ፩፤፵፪)። እርሱ ቡሩክ ሳለ ማለትም መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለበት መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሚያርቅ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ የሚያድል ሆኖ ሳለ «በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተገመ ነው ተብሎ ተጽፏልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን» (ገላ ፫፤፲፫) ተብሎ እንደተጻፈ ስለ እኛ ተሰቅሎ ከእርግማን አዳነን። እግዚአብሔርም በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ በምድራውያንና በሰማያውያን በረከት ባረከን (ኤፌ ፩፤፫,፬)። ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለተኛ ሲመጣ ከተባረከችው ድንግል የተወለደውን ቡሩኩን የማሕጸንዋን ፍሬ አምኖ በመስቀሉ እርግማኑ የተወገደለት መሆኑን በእርግጠኝነት የተቀበለ «እናንተ የአባቴ ቡሩካን ወደ እኔ ኑ» (ማቴ ፳፭፤፴፬) ብሎ ከሚጠራቸው ጋር ይቆጠራል። «በክርስቶስ በሰማያዊ ሥፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባትና አምላክ ይባረክ» (ኤፌ ፩፤፫)።

### ምእመናንና እመቤታችን

ምእመናን እመቤታችንን ይወዷታል ያከብሯታል «ትምክህተ ኩልነ ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ - አምላክን የወለድሽ እመቤታችን መመኪያችን ነሽ» እያሉ ያወድሷታል። ምክንያቱም ግልጽ ነው። አምላክን የወለደች የሰው ልጆች የባሕርይ ትምክህት የሆነውን ጌታ ስለተሸከመች ኅብስተ - ሕይወት የሕይወት እንጀራ ከእርሷ ስለተገኘ ብርሃነ ሕይወት ከእርስዋ ስለወጣ ሐረገ ወይን ከእርሷ ስለበቀለ ማየ ሕይወት ከእርሷ ስለመነጨ እግዚአ አጋእዝት የእርሷ ልጅ ስለሆነ ነው። በሌላም በኩል ከእግረ መስቀሉ ስለተሰጠቻቸው ምእመናን ያወድሷታል።

በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የምናምን ሁላችን ድንግል እናታችን መሆንዋን ልናምን ያሻል። እነኋት እናትህ ብሎ ለዮሐንስ ሲሰጥ ዮሐንስን ለመሰልን እናት ሆናናለችና፤ እነሆ ልጅሽ ብሎ ዮሐንስን ሲሰጣትም ልጆችዋ ሆነናልና (ዮሐ ፲፱፤፳፮)። ከዚያም በላይ በጸሎትዋ ይማጸናሉ «ሰዐሊ ለነ ቅድስት» በማለትም ጸሎትዋን ይሻሉ «በእንተ ማርያም ጸዋሪትከ በእንተ ማርያም ሃጸኒትከ፤ በእንተ ማርያም ወላዲትከ» በማለት ይጸልያሉ፤ ሕዋሳቶችዋንም ማላጅ በማድረግ ስለተሸከመህ ስለማሕጸንዋ፤ ስለጠባሃቸው ስለጡቶችዋ፤ ስለአዩህ ስለዓይኖችዋ፤ በፊትህ ስለፈሰሰው ስለእንባዋ ይቅር በለን ይላሉ። ስለ እናቱ ይቅር ይበለን።

### ዕረፍተ ድንግል

መተርጉማን አበው እንደሚተርኩት እመ እግዚአብሔር ጸባኦት ድንግል ማርያም በተወለደች በስልሳ አራት ዓመትዋ በዘመነ ሉቃስ ጥር ፳፩ ቀን አርፋለች። አበው ስለ ዜና እረፍቷ የሚተርኩበት ትርጉሜ ውዳሴ ማርያም እንደገለጸው የድንግል ማርያም እድሜ ፷፬ ሊሆን የቻለው ከወላጆችዋ ጋር ፫ ዓመት በቤተ መቅደስ ፲፪ ዓመት፣ በቤተ ዮሴፍ ፱ ወር፣ ከጌታ ኢየሱስ ጋር ፴፫ ዓመት ከሦስት ወር፣ ከጌታ ሞት በኋላ በቤተ ዮሐንስ ፲፭ ዓመት ስለተቀመጠች እድሜዋ ተገናኝቶ ፷፬ ዓመት ይሆናል። የእርሷን ስም የሚገልጹ የውዳሴ ጽሑፎችም በእድሜዋ ልክ ተደርሰዋል። ለምሳሌ የውዳሴ ማርያም ቁጥር ፷፬ ነው፤ የመልክአ ማርያም ቁጥርም ፷፬ ነው።

የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ምልጃዋና ልመናዋ ዘወትር አይለየን … አሜን።